# የብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐውልት ፡ ምረቃ ፡

## ሐምሌ ፡ ፳፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ.ም.

ከትምህርትና ፡ የሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ታተመ ።

ተሐትመ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ በ፲፮ ፡ ዓመቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡
ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ. ም.

---

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።
፲፱ ፲፩ ፴፰ ቍ. [illegible] መ ፲፻ ።

www.ethiopianorthodox.org

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911860113
0111/271689
D.N Solomon Yohannes

# የብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐውልት ፡ ምረቃ ፡

## ሐምሌ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ. ም.

ከትምህርትና ፡ የሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ታተመ ።

STUDENTS ASSOCIATION

ተነትመ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ በ፲ቱ ፡ ወ፮ቱ ፡ ዘመን ፡ መንግሥቱ ፡ ለቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ. ም.

---

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ፤
፲፱ ፲፭ ፵፰ ቍ. ፱፻፷፮፻፶፯ መ. ፲፫ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ማውጫ ።


፩ ፣ የብፁዕ ፣ አቡነ ፣ ጴጥሮስ ፣ የሕይወታ
ቸው ፣ ታሪክ ።　.　.　.　.　.　ገጽ ፫

፪ ፣ ግርማዊ ፣ ቀዳማዊ ፣ ኃይለ ፣ ሥላሴ ፣ ንጉሠ ፣ ነገሥት ፣
ዘኢትዮጵያ ፣ የብፁዕ ፣ አቡነ ፣ ጴጥሮስን ፣ መታሰቢያ ፣
ሐውልት ፣ ሲገልጡ ፣ የተናገሩት ፣ ቃል ።　ገጽ ፲፩

፫ ፣ ስለ ፣ ግርማዊ ፣ ንጉሠ ፣ ነገሥት ፣ ቀዳማዊ ፣ ኃይለ ፣
ሥላሴ ፣ ፵፬ኛ ፣ ዓመት ፣ የልደት ፣ በዓል ፣ አከባበር ፣
የከተማው ፣ ገዥ ፣ የተናገሩት ፣ ቃል ።　ገጽ ፳፫


www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

## ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኢ.ትዮጵያዊ ።

ይህ ፡ ሐውልት ፡ በ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ. ም ፡ ሐምሌ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ግፈኛው ፡ ጠላታችን ፡ የኢጣልያ ፡ ፋሺስት ፡ የገደላቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰማዕት ፡ የብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ መታሰቢያ ፡ ሆኖ ፡ በ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ. ም. ሐምሌ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ቆመ ።

## ልደትና ፡ አስተዳደግ ።

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ በ፲፰፻፹፬ ፡ ዓ. ም. ሰላሌ ፡ በፍቼ ፡ ከተማ ፡ ) ተወለዱ ። ገና ፡ ሕፃን ፡ ሳሉ ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ ወስደው ፡ ከባሕታዊ ፡ ተድላ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ አስገቧቸው ። በዚያም ፡ ለጀማሪዎች ፡ የተመደበውን ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ትምህርት ፡ እየተማሩ ፡ አደጉ ። ስማቸው ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ነበር ።

## በትምህርት ፡ ቤት ።

ገና ፡ ወጣት ፡ ሳሉ ፡ ቅኔ ፡ ተምረው ፡ ተቀኙ ። እንደ ፡ ገናም ፡ ወደ ፡ ዋሸራ ፡ ሄደው ፡ ለመምርነት ፡ የሚያበቃውን ፡ ትምህርት ፡ ፈጽመው ፡ ለቅኔ ፡ አስተማሪነት ፡ ተመረቁ ። ጥቂት ፡ ዘመን ፡ በጎንደር ፡ ዜማ ፡ ቀጸሉ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ወሎ ፡ (በሩ ፡ ሜዳ ፡ )ላይ ፡ ከታላቁ ፡ ሊቅ ፡ ከመምህር ፡ አካለ ፡ ወልድ ፡ ብሉያትንና ፡ ሐዲሳትን ፤ ሊቃው

www.ethiopianorthodox.org

ንትም ፡ አሄዱ ። ባ፲፱፻ ፡ ዓ. ም. ከምስካበ፡ቅዱሳን፡ገዳም፡ (አማራ ፡ ሳይንት ፡ )ገብተው ፡ ፱ ዓመት ፡ ቅኔና ፡ መጻሕ ፍትን ፡ አስተማሩ ።

## ም ን ኵ ስ ና ።

ባ፲፱፻፱ ፡ ዓ. ም. በደብረ ፡ ሊባኖስ፡ገዳም፡መነኰሱ ። ወዲያው ፡ ማዕርገ ፡ቅስና ፡ ተቀብለው ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ተልዕኮ ፡ ያዙ ። ባ፲፱፻፲ ፡ ዓ. ም. በወላሞ፡ወረዳ፡ለደብረ፡ መንክራት ፡ ገዳም ፡ መምህር ፡ ተብለው ፡ ከደበረ ፡ ሊባ ኖስ ፡ ተሾሙ ። ባ፲፱፻፲፮ ፡ ዓ. ም. በዝዋይ ፡ ደሴት ፡ የገዳሙ፡መምህር፡ ሆኑ ። ባ፲፱፻፲፱ ፡ ዓ. ም. አዲስ፡አበባ፡ ላይ ፡ የመንበረ ፡ ልዑል፡ ማርቆስ ፡ መምህርና፡በቤተ፡መን ግሥት ፡ የግርማዊነታቸው ፡ አበ ፡ ንስሓ ፡ ሆኑ ።

## ጵ ጵ ስ ና ።

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ (ግርማዊ፡ንጉሥ፡ተፈሪ፡እየተባሉ፡ሳሉ፡) ባ፲፱፻፳፩ ፡ ዓ. ም. አራት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መነኰሳት፡ በእስክንድርያ ፡ በቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ መንበር ፡ ካለው ፡ ፓትሪያርክ ፡ ጵጵስና ፡ እንዲሾሙ ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፡ ከተመ ረጡት ፡ መነኰሳት ፡ አንደኛው ፡ መምህር ፡ ኃይለ ፡ ማር ያም ፡ ናቸው ። በግንቦት ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ የጵጵናውን ፡ ማዕ ርግ ፡ ሲቀበሉ ፡ ስማቸው ፡ «ጴጥሮስ» ፡ ተብሎ፡ተሰየመ ።



ከኢትዮጵያ ፡ አውራጆች ፡ የደረሳቸው ፡ ሀገረ ፡ ስብከት ፡ መንዝና ፡ ወሎ ፡ ነበር ።

## አ ር በ ኝ ነ ት ።

አረመኔው ፡ የኢጣሊያ ፡ ፋሺስት ፡ ባ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ. ም. በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የግፍ ፡ ጦርነትን ፡ ባነሣ ፡ ጊዜ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ከጦር ፡ ስፍራ ፡ ለመለየት ፡ ስለ ፡ አልሆነላቸው ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትን ፡ ተከ ትለው ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ ዘመቱ ፤ ጠላ ታችን ፡ የኢጣሊያ ፡ ፋሺስት ፡ ማይጨው ፡ ላይ ፡ የመ ርዝ ጦርነት ፡ ከማድረጉ ፡ የተነሣ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሠራ ዊት ፡ ሲበታተን ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለሱ ። በሚያዝያ ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ደብረ፡ ሊባኖስ ፡ ሄደው ፡ ለሀገርና ፡ ለነጻነት ፡ መሞት ፡ ቅዱስ፡ ተግባር ፡ መሆኑን ፡ ለሰላሌ ፡ አርበኞች ፡ ይሰብኩ ፡ ጀመር ። የሰላሌ ፡ አርበኞች ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ዘም ተው ፡ በ፳፩ ፡ ሐምሌ ፡ ጠላትን ፡ ሲወጉት ፡ እሳቸውም ፡ በመካከላቸው ፡ ነበሩ ።

## በ ጠ ላ ት ፡ እ ጅ ።

ጠላትን ፡ ለመውጋት ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ የዘመ ቱት ፡ የሰላሌ ፡ አርበኞች ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዲመለሱ ፡ የጠ ላት ፡ ኃይል ፡ ባስገደዳቸው ፡ ጊዜ፡አቡነ ፡ ጴጥሮስ፡ፊቴን፡ አላዞርም ፡ ብለው ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፤ ቀሩ ። በሐምሌ፡፳፪



www.ethiopianorthodox.org

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911660113
0111271609
D.N Solomon Yohannes



ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ

ረቡዕ ፡ ወደ ፡ ራስ ኃይሉ ፡ ተ ፡ ሃ ፡ ቤት ፡ ሄደው ፡ ይኸው ፡ አለሁ ፡ ብለው ፡ አስታወቁ ። የፋሺስቶች ፡ አለቃ ግራሲያኒ ፡ ወዲያው ፡ አስጠርቶ ፡ ለኢጣሊያ ፡ ንጉሥ ፡ ተገዢ ፡ ነኝ ፡ እንዲሉ ፡ በማስፈራራት ፡ ሲጠይቃቸው ፤ እንዲህ ፡ ብለው ፡ መለሱለት ፤ «ሰማያዊ ፡ ንጉሢ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፤ ምድራዊ ፡ ንጉሢም ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ኢትዮጵያ ፡ የኢትዮጵውያን ፡ ናት» ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግራሲያኒ ፡ እንደ ፡ ሽፍታ ፡ ግደሉት ፡ ብሎ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠ ።

## በሞት ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ በፋሺስት ፡ ወታደሮች ፡ ተይዘው ፡ ወደሚገደሉበት ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ አራዳ ፡ ገበያ ፡ ተወሰዱ ። ሲገደሉ ፡ ለማሳየት ፡ ፋሺስቶች ፡ ሕዝቡን ፡ ሰበሰቡት ። አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ከሚገደሉበት ፡ ስፍራ ፡ ሲደርሱ ፡ አራቱን ፡ ማዕዘን ፡ በመስቀላቸው ፡ ባረኩ ፤ በሕዝቡም ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፤ «ፋሺስቶች ፡ የሀገራችንን ፡ አርበኞች ፡ ሽፍታ ፡ ቢሏቸው ፡ እውነት ፡ አይምሰላችሁ ፤ ሽፍታ ፡ ማለት ፡ ያለ ፡ ሀገሩ ፡ መጥቶ ፡ የሰውን ፡ ርስትና ፡ ከብት ፡ የሚቀማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ የሚቃጠል ፤ የክርስቲያንን ፡ ደም ፡ የሚያፈስ ፤ ይህ ፡ በመካከላችሁ ፡



www.ethiopianorthodox.org

የቆመው ፡ አረመኔው ፡ የኢጣሊያ ፡ ፋሺስት ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ለሱ ፡ እንዳይገዛ ፡ ውጉዝ ፡ ነው ። የኢትዮጵያም ፡ መሬት ፡ እንዳትቀበለው ፡ የተገዛች ፡ ትሁን» ፡ ብለው ፡ ተናግረው ፡ ሲጨርሱ ፤ በመትረየስ ፡ ተኩሰው ፡ ገደሏቸው ።

---

## የጻድቅ ፡ መታሰቢያ ፡ ለዘላለም ፡ ይኖራል ።

«ጴጥሮስ ፤ ስምህ ፡ የማይሞት ፡ ሕያው ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ሐውልት ፡ የብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስን ፡ ስምና ፡ ታሪክ ፡ ያስተባብራል ። አንተ ፡ መሠረት ፡ ነህ ። በንተ ፡ መሠረትነት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ እንጻለሁ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፤ ለብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ የምናቆመውን ፡ ሐውልት ፡ ስለ ፡ ሀገራቸው ፡ የተሠዉ ፡ ኢትዮጵያኖች ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ለሚቆምላቸው ፡ መታሰቢያ ፡ እንደ ፡ መጀመሪያ ፡ መሠረት ፡ አድርገን ፡ እንቈጥረዋለን ። »

ሐምሌ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ. ም.

ቀ. ኃ. ሥ.



ሐምሌ ፡ ፲፯/ ፴፰ ፡ ዓ. ም.

ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፤
የብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስን ፡ መታሰቢያ ፡ ሐውልት ፡ ሲገልጡ ፡
የ ተ ና ገ ሩ ት ፡ ቃ ል ።

የአጥቂ ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ በኢትዮጵያ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ በጽኑ ፡ ፈቃድ ፡ አልገዛም ፡ በማለትና ፡ ስለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ለመከላከል ፡ በሰማዕትነት ፡ ሕይወታቸውን ፡ የሰጡትን ፡ አንደኛውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ አርበኛ ፡ መታሰቢያ ፡ በዚህ ፡ በመገኘት ፡ ለማክበር ፡ ዛሬ ፡ ተሰብስበናል ።

ይህ ፡ በፊታችን ፡ ቆሞ ፡ የምንመለከተው ፡ ሐውልት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጳጳስ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ በሐምሌ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፰ ዓመት ፡ የተገደሉበትን ፡ ቦታ ፡ ያሳየናል ። አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ የተገኘባቸው ፡ ወንጀል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጳጳስና ፡ በሚገባቸው ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሳያፈገፍጉ ፡ የተገኙ ፤ በዓለም ፡ ፊት ፡ በፋሺስትና ፡ በግራሲያኒ ፡ ሕገ ፡ ውጡ ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ የፈረዱ ፡ መሆናቸው ፡ ነው ።

ፋሺስት ፡ ሊያጠፋቸው ፡ ከሚፈልጋቸው ፡ ኢትዮጵያውች ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስን ፡ ሲገድል ፡ አጥቂው ፡ ጠላታችን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ትምህርትና ፡ መልክም ፡ ምግባር ፡ ከመ



www.ethiopianorthodox.org

ሠረቱ፡ አናግቶ፡ ለመገልበጥ፡ የቱን፡ ያህል፡ እንዳሰበበት፡ የሚያመለክት፡ ነበር። ደግሞ፡ በንጉሡ፡ ነገሥት፡ መንግሥት፡ ግዛታችን፡ በያለበት፡ አብያተ፡ ክርስቲያኖችን፡ ሆነ፡ ብሎ፡ በማቃጠል፡ በተለየ፡ ላደረገው፡ የጨካኝነት፡ ሥራው፡ መረጃሚያ፡ ይህ፡ መሆኑን፡ የሚያሳይ፡ ነበር።

ዛሬ፡ መታሰቢያቸውን፡ ከምናከብርላቸው፡ ጳጳስ፡ መገደል፡ በፊት፡ ስለ፡ ፈረሱት፡ አብያተ፡ ክርስቲያናት፡ ስለ፡ ተዘረፈውና፡ ስለ፡ ጠፋው፡ ንዋየ፡ ቅድሳት፡ የመንግሥታት፡ ማኅበርና፡ የቀይ፡ መስቀል፡ ማኅበር፡ የሠለጠኑም፡ የዓለም፡ ሕዝብ፡ ይመሰክራሉ። ከዚህም፡ በቀር፡ ባዶሊዮ፡ በጥር፡ ወር፡ ፲፱፻፳፰ ዓመት፡ በወጣው፡ በቃሪክ፡ መዝገብ፡ በገባው፡ ማስታወቂያ፡ ይህንኑ፡ የጦር፡ ወንጀሉን፡ ገልጦ፡ ስለ፡ ተናገረ፡ ለዚህም፡ ምስክሮች፡ ናቸው።

አቡነ፡ ጴጥሮስ፡ በመገደላቸው፡ ጠላት፡ በተከለከለ፡ መሣሪያ፡ በመርዝ፡ ጢስ፡ የተዋጋበት፡ ከተማና፡ ቤት፡ ያቃጠለበት፡ ከጦር፡ ግንባር፡ የሌሉትን፡ ሽማግሌችና፡ ሴቶች፡ የፈጀበት፡ በማስጨነቅና፡ በማስደንገጥ፡ የሕዝባችንን፡ ምግባር፡ ያጠፋበት፡ የተማሩትን፡ ወጣቶች፡ የፈጀበት፡ ተማሪ፡ ቤቶችን፡ በፍጹም፡ ያፈረሰበት፡ ዋና፡ ምክንያት፡ ተገለጠ። ብ፲፱፻፳፱፡ ዓመት፡ የተደረገውን፡ ኀልቀት፡ ለሕዝባችን፡ ልብ፡ አሰማው። ሁሉም፡ ተራ



ውን፡ ይጠብቅ፡ ጀመር። አባ፡ ጴጥሮስ፡ ከተገደሉበት፡ ቀን፡ በኋላ፡ የፋሺስት፡ አስተዳዳሪዎች፡ በሕዝባችን፡ ላይ፡ እንደጌጥ፡ አድርገው፡ ለፈጸሙበት፡ የጨካኝነት፡ ሥራ፡ የውጪ፡ አገር፡ ሕዝቦች፡ ምስክሮች፡ ናቸው። ለዚህም፡ የጨካኝነት፡ ሥራ፡ መጠን፡ በሕይወታቸው፡ ስንኩል፡ ሆነው፡ የቀሩ፡ ስንት፡ ሰዎች፡ ምስክሮች፡ ናቸው።

ይህ፡ ሁሉ፡ ከተደረገ፡ በኋላ፡ ጠላት፡ በአጥቂነት፡ ኢትዮጵያን፡ በወረረ፡ ጊዜ፡ ሀብት፡ አምጥቼለታለሁ፡ ብሎ፡ ዛሬ፡ ሲናገር፡ ይሰማል። በኢትዮጵያ፡ የገንዘብና፡ የቆመ፡ ሀብት፡ አምጥቻለሁ፡ ማለቱ፡ እንደሆነ፡ አምጥቻለሁ፡ የሚለውንና፡ በአገር፡ ውስጥ፡ ያጠፋውን፡ ኢትዮጵያ፡ ከመወረሩዋ፡ በፊት፡ በዚህ፡ የነበሩ፡ ለማመዛዘን፡ ይችላሉ። ጠላት፡ በኢትዮጵያ፡ በወራሪነት፡ በገባ፡ ጊዜ፡ ጦርነቱን፡ በአጥቂው፡ ላይ፡ ሳያቋርጥ፡ ከቀጠለው፡ ከኢትዮጵያ፡ ሕዝብ ለመከላከል፡ ለጦር፡ አገልግሎት፡ የሚሆኑ፡ የማይቈዩ፡ ነገሮች፡ በመጣደፍ፡ ሠራ፡ እንጂ፡ ለአገሩ፡ ሀብትና፡ እድገት፡ የሚሰጥ ነገር፡ አላደረገም። ጠላት፡ በኢትዮጵያ፡ አመጣሁ፡ የሚለው፡ ሀብት፡ በአእምሮና፡ በመልካም፡ ተግባር፡ ረገድ፡ እንደሆነ፡ ኢትዮጵያዊ፡ የሆነ፡ መንፈስ፡ የፋሺስት፡ አገዛዝ፡ የቱን፡ ያህል፡ ውርደትና፡ ርኵሰት፡ የሚያመጣ፡ መሆኑን፡ ለመዘርዘር፡ ሲያስብ፡ አእምሮው፡ የሚናወጥ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ለዚህ፡ ምላ



www.ethiopianorthodox.org

ሹን ፡ ለመስጠት ፡ ባሥር ፡ ዓመት ፡ ጦርነት ፡ ለተፈተ
ነው ፡ ለዓለም ፡ ሕዝብ ፡ ሕሊና ፡ እንተወዋለን ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የነበረውን ፡ የዓለም ፡ አኳሆን ፡ ስና
ስብ ፡ ይህን ፡ የጨካኝነትና ፡ በንግግር ፡ ሊገለጥ ፡ የማይቻ
ለውን ፡ መከራ ፡ ጠላት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ሲያወርድ ፡
በትዕግሥት ፡ የታለፈበትን ፡ በሐተታ ፡ ለማስረዳት ፡ የሚ
ያሳዝን ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ከሰው ፡ ልጅ ፡ መል
ካም ፡ ተግባር ፡ የተለየ ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ ዓለም ፡ አልቀበ
ልም ፡ ቢልና ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ሕግ ፡ ሲጣስ ፡ በኃ
ይል ፡ ቢቃወም ፡ ባለፉት ፡ ባሥር ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ቍጥ
ራቸው ፡ መጠን ፡ የሌለውን ፡ የሞቱትን ፡ ሰዎችና ፡ ለመ
ሥዋዕትነት ፡ የተሰጡትን ፡ ሁሉ ፡ ለማዳን ፡ ሳይቻል ፡
ይቀር ፡ ኖሩዋልን ።

ይህ ፡ አሁን ፡ የምንመለከተው ፡ ሐውልት ፡ ምንም ፡
ከአውሮፓ ፡ የጦር ፡ ሜዳ ፡ የራቀ ፡ ቢሆን ፤ በመሠረታዊ ፡
ታላቅነቱ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛቶችን ፡
ወሰንና ፡ የመላ ፡ የአፍሪቃን ፡ ዓለም ፡ አልፎ ፡ በኢትዮ
ጵያ ፡ የወደቁትን ፡ የኢትዮጵያንና ፡ የብሪታንያ ፡ ጀግኖች ፡
በኤልአላሜ ፤ በሳሌርን ፤ በስታሊንግራድ ፡ በኖርማንዲ ፤
በአኪናዋ ፤ ከወደቁት ፡ ጀግኖች ፡ ጋራ ፡ የሚያስተሳስር ፡
ነው ።

የሰላም ፡ ጉባኤ ፡ ወደፊት ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ሊደረግ ፡
ነው ። ኢትዮጵያ ፡ በስልሳ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡



መከራ ፡ ያመጣባትን ፡ ጠላት ፡ በታላቅ ፡ ትዕግሥት ፡ ተሸ
ክማ ፡ መኖርዋን ፡ አስረድታለች ። አሁንም ፡ ብዙ ፡ ሺ ፡ የጠ
ላት ፡ ዜጎች ፡ በአገራችን ፡ በሰላማዊ ፡ ኑሮ ፡ ይኖራሉ ፤
በአጥቂ ፡ ጠላት ፡ የተበደለችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከዑንራ ፡
ማኅበር ፡ ያገኘችው ፡ ርዳታ ፡ ምንም ፡ ከቍጥር ፡ የማይገባ ፡
ቢሆን ፡ በጦርነት ፡ ምክንያት ፡ የተጎዱትን ፡ አገሮች ፡ ለማ
ቋቋም ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ላቆመው ፡ ማኅበር ፡ ርዳታ ፡
እንዲሰጥ ፡ በተባለ ፡ ጊዜ ፡ ነገሩን ፡ ደግፈን ፡ ረድተናል ።
የዓለም ፡ አንድነት ፡ ማኅበረተኞች ፤ በመሆናችን ፡ ከወ
ትሮ ፡ ጠላቶቻችንም ፡ ጋራ ፡ ቢሆን ፡ በሰላም ፡ እየሠራን ፡
ለመኖር ፡ በመሠረቱ ፡ ተስማምተን ፡ የምንቀበለው ፡ ነው ።
ስለሆነ ፡ ይህ ፡ የመረዳዳት ፡ ሰላማዊ ፡ ሥራ ፡ ከሁለቱም ፡
ወገን ፡ በመልካም ፡ ሃይማኖትና ፡ በመተማመን ፡ ላይ ፡
እንዲመሠረት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፡ ላደረገ
ችው ፡ ለመተማመንና ፡ ለመረዳዳት ፡ ሥራ ፡ ምንም ፡ የም
ትጠብቀው ፡ ነገር ፡ ባይደርስላት ፡ ከዚህም ፡ ቀድሞ ፡ በመ
ልካም ፡ ሃይማኖት ፡ አድርጋለች ፤ አሁንም ፡ ወደፊት ፡ ይህ
ንኑ ፡ ከማድረግ ፡ አታቋርጥም ። አሁን ፡ አጥቂ ፡ ለሆነው ፡
ጠላት ፡ የሚቀረው ፡ በወዳጅነት ፡ እጁን ፡ መዘርጋት ፡
ነው ። ስለሆነ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ወዳጅነት ፡ ለማግኘት ፡ የፈ
ለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለፈው ፡ ባደረገው ፡ ከፍርድ ፡ በወጣ ፡
ሥራው ፡ ከልብ ፡ መጸጸትና ፡ በጥፋቱም ፡ ለመካስ ፡ የተ
ዘጋጀ ፡ መሆኑን ፡ መግለጥ ፡ ያስፈልገዋል ። ጠላታችንም



www.ethiopianorthodox.org

ይህን ፡ ሲያደርግ ፡ በስልሳ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ በሁለታችን ፡ መካከል ፡ የነበረውን ፡ መገናኛ ፡ ገልጠ ፡ ያሳየውን ፡ በኢጣልያ ፡ በኩል ፡ የተደረገውን ፡ የጥቂትነት ፡ አሳብ ፡ ፍቆ ፡ በሰላም ፡ ለመሥራት ፡ መተማመንና ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ የጨመረበት ፡ እንደሆነ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በወዳጅነትና ፡ በመገባባት ፡ የምትቀበለው ፡ ይሆናል ።

አሁን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ወደ ፡ ደረስንበት ፡ ወደ ፡ ሰላሙ ፡ ዘመን ፡ አሳባችንን ፡ እንመልስ ። ይህም ፡ በጽኑ ፡ መሠረት ፡ የዓለም ፡ ሰላም ፡ እንዲመሠረትበት ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ የሚደክሙበት ፡ ሰላማዊ ፡ ዘመን ፡ የሚጣልለት ፡ መሠረት ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ የማይናወጥ ፡ እንዲሆን ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ በንጹሕ ፡ ደንጊያ ፡ ያለማድላት ፡ እንዲመሠርቱት ፡ ያስፈልጋል ።

ሰላም ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ ለማድረግና ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በዕለት ፡ ተግባሩ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ የኑሮ ፡ ዕረፍትን ፡ እንዲያገኝ ፡ አሁን ፡ ሊጣል ፡ የታሰበው ፡ የሰላም ፡ መሠረት ፡ ለትንሽ ፤ ለትልቅ ፡ ሳይል ፡ ከሕሊናና ፤ ከእውነተኛ ፡ ፍርድ ፡ ጋራ ፡ የተስማማ ፡ ሲሆን ፡ ለሚመጣው ፡ ትውልድ ፡ መልካም ፡ አኑዋኑዋር ፡ የማያልቅ ፡ ሀብት ፡ የሚተውለት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

ይህ ፡ ብቻ ፡ አይበቃም ። በተለየ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ እንድንሠራ ፡ ያለብን ፡ ተግባር ፡ ተስፋ ፡ እንደምናደርገው ፡



በሕሊናና ፡ በእውነተኛ ፡ ፍርድ ፡ የሚመሠረተውን ፡ ሰላም ፡ የሚመጣው ፡ ትውልድ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ መሥዋዕትነት ፡ የፈጀ ፡ መሆኑን ፡ ተረድቶ ፡ ዋጋው ፡ እንዳይጠፋ ፡ ማድረግ ፡ የተገባው ፡ ነው ። ይህም ፡ ማመዛዘኛ ፡ የሚገኘው ፡ በትምህርት ፡ ነው ።

ኢትዮጵያ ፡ ወግና ፡ ማዕርግ ፡ ያለው ፡ ታሪካዊ ፡ሥልጣኔ ፡ በመያዝ ፡ ቀደምትነት ፡ አላት ፤ ስለሆነ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጓደኞቿዋ ፡ በከፍተኛው ፡ ሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ለመገኘት ፡ ዘመናዊ ፡ ሥልጣኔን ፡ መከተል ፡ እንዳለባት ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሊሆንባት ፡ አይችልም ። በሩም ፡ በሰፊው ፡ ቀክፍቶላታል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከሥልጣኔዋ ፡ ጋራ ፡ አዋሕዶ ፡ በሚጠቀማት ፡ ረገድ ፡ ዘመናዊን ፡ ሥልጣኔ ፡ ለማግባት ፡ ማበጠሪያ ፡ የሆነውን ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ያስፈልጋታል ።

ጠላት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከመውረሩ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በገራችን ፡ ማስፋፋት ፤ ምንም ፡ በተለየ ፡ ሁላችሁም ፡ የምታውቁት ፡ የሚያቋርጥ ፡ ችግር ፡ ቢደርስብን ፡ በተቻለ ፡ ደክመንበታል ፤ የተማሪ ፡ ቤትም ፡ ፍሬዎች ፡ በሰላሙም ፡ በኢትዮጵያም ፡ መከራ ፡ ጊዜ ፡ ሥራቸውን ፡ አሳይተዋል ። በጠላት ፡ እየተበረበሩና ፡ እየተለቀሙ ፡ የተጨረሱትን ፡ እናስታውሳለን ።



www.ethiopianorthodox.org

ሰው ፡ በተፈጥሮው ፡ የአሳብ ፡ ነጻነት ፡ ሲሰጠው ፡ ይህ ፡ ነጻነቱ ፡ ራሱን ፡ ወደ ፡ ማስቻል ፡ እንዲያደርሰው ፡ የአሳቢነቱ ፡ አእምሮ ፡ በትምህርት ፡ እንዲታነጽ ፡ ያስፈልጋል ። እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በትምህርት ፡ በጐለመሰ ፡ አእምሮ ፡ ራሱን ፡ መቻል ፡ የመላውን ፡ ያገር ፡ ራስ ፡ መቻልና ፡ ነጻነት ፡ የሚያስከትል ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ዛሬ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተቋቁመው ፡ የምናያቸውን ፡ ተማሪ ፡ ቤቶች ፡ ቍጥር ፡ በቀድሞው ፡ ስናስተያየው ፡ ብልጫው ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘን ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ ያሁኑ ፡ ትውልድ ፡ ትምህርት ፡ በመናፈቁ ፡ እንዲማር ፡ የምናስበው ፡ እለሰለሰ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ስለሚዘራ ፡ የሚያኰራን ፡ ነው ።

በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በብዙ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ተማሪ ፡ ቤቶች ፡ ቆመው ፡ እንደዚሁም ፡ በብዙ ፡ ሺ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ተማሪዎች ፡ ይገኙበታል ። ከነዚሁም ፡ ተማሪዎች ፡ መካከል ፡ ኢትዮጵያን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ለማገልገል ፡ ለመቻላቸው ፡ ችሎታቸውን ፡ የገለጡ ፡ ቍጥራቸው ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ ወጣቶች ፡ ይታይባቸዋል ።

ከነዚሁም ፡ በጠባያቸው ፤ በትምህርታቸውና ፡ በትጋታቸው ፡ የሚመረጡት ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ ተልከው ፡ ትምህርታቸውን ፡ እንዲፈጽሙ ፡ ይደረጋል ። ከዚህም ፡



በቀር ፡ ለሕዝባችን ፡ መልካም ፡ ማስተዳደሪያ ፡ የወታደር ፤ የፖሊስ ፤ የአውሮፕላን ፡ ተማሪ ፡ ቤቶች ፡ ቆመዋል ።

የኢትዮጵያ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ ብቻ ፡ የሚወሰን ፡ አይደለም ። በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ታላቅ ፡ ኡኒቬርሲቲ ፡ እንዲከፈት ፡ ተዘጋጅቷል ። በብዙ ፡ ሺ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ተጨማሪ ፡ ተማሪ ፡ ቤቶች ፡ እንዲቋቋሙ ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ የምንደክምበት ፡ ነው ።

መማር ፤ መሥራት ፤ መትጋት ፡ የነጻነት ፡ ዋና ፡ መሠረት ፡ ስለሆነ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የሆንህ ፡ ሁሉ ፡ ልጅህን ፡ በያጠገብህ ፡ ባለው ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ አስተምር ፤ ልጁን ፡ ያላስተማረ ፡ ራሱን ፡ እንደ ፡ መግደል ፡ የሚያስቈጥር ፡ ነው ።

ባለፉት ፡ ዓመታት ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ የመጣውን ፡ መቅሠፍት ፡ ወደፊት ፡ ለማስጣል ፡ የሚቻለው ፡ በሃይማኖትና ፡ በተስፋ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ አድራ ፡ በሚጣል ፡ በሕዝብ ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህም ፡ በትምህርት ፤ በጐለመሰ ፡ አእምሮ ፡ ካልተያዘ ፡ የሚጣለው ፡ የሰላም ፡ መሠረት ፡ ከንቱ ፤ ሆኖ ፡ እንዳይቀር ፡ ያሠጋል ።

በቅርብ ጊዜ ፡ ለሚደረገውም ፡ ለሰላም ፡ ጉባኤ ፡ ፍርድ ፡ የማይጣስበትን ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ መብት ፡ የማይጐድልበትን ፡ ለማከናወን ፡ እንዲችል ፡ ብርሃኑን ፡ እንዲገልጥለት ፡ እንመኛለን ።



www.ethiopianorthodox.org

## SPEECH OF HIS IMPERIAL MAJESTY ON THE OCCASION OF THE UNVELING OF THE MONUMENT TO THE MEMORY OF ABUNA PETROS 23rd JULY, 1946.

———///———

*We have met today to commemorate by Our presence the martyrdom of an Ethiopian patriot who consecrate with his blood the place where we now stand, in defence of the principles of religion and of uncompromising resistance against the forces of aggression.*

*The Monument which We have unveiled, distinguishes the square where the Church Leader, Abuna Petros, was shot by the Italian aggressors in July 1936. His crime was that of being Ethiopian and a leader of the Ethiopian Church, a leader that shrank not from condemning before the world the immorality of the Fascist and Graziani's regime.*

*His death which had been ordered amongst the first of those sought by the Fascists, marked the importance which the aggressor attached to the destruction of the basis of Ethiopian culture and standards of conduct. It also marked the culminating point in the bitter struggle in the course of which the enemy systematically burned and destroyed churches throughout Our Empire. The League of Nations and the International Red Cross as well as the civilised nations were witnesses to the widespread destruction of churches and the plundering of religious objects and shrines in Ethiopia. They were likewise witnesses to the confession to those same atrocities published as early as January 1936 by that war criminal Badoglio.*



*The death of Abuna Petros marked a significant point in a struggle characterised by the use of proscribed means of warfare, such as poison gas, the burning of villages and homes, the murder of non-combattants and the old, and by the attempt systematically to abase the moral standards and the culture of the country through terrorism, the slaughter of the educated classes and the total destruction of schools. His death likewise preceded the massacres of February 1937 and those that followed. The World was also witness to the brutality, lust and orgy which characterised the Fascist regime in the long*



www.ethiopianorthodox.org

months following the death of Abuna Petros. How many victims bear witness here today with broken lives to the depths of those atrocities?

In the teeth of this record, the enemy today, in callous cynicism seeks to justify his crimes by pointing to benefits which he claims to have brought to Ethiopia. If he speaks of material benefits, those who have been here before the invasion and who are in position to establish a comparison can place a proper evaluation upon that claim. The enemy built frantically in order to defend himself against a nation that refused resolutely to lay down its arms against the aggressor; he did not build in order to bring any permanent contribution to the country. If the enemy has, rather, the effrontery to refer to moral values, We leave to World conscience chastened by ten years of war the duty of replying, since Ethiopia refrains from detailing the degradation which the Fascist regime brought to the country.

It is a sad commentary on the state of the world of that period which tolerated the brutalities and the campaigns of unspeakable atrocities in Ethiopia. We ask, had the world refused to tolerate those immoralities, if it had reacted with energy against those violations of international law, might we not have been spared the countless deaths and sacrifices of the last ten years?



This monument, although far from the battlefields of Europe, has, therefore, a significance that transcends the frontiers of Ethiopia and the confines of the Continent of Africa and unites the dead of Ethiopia, the Ethiopian and British heroes, with those of El Alamein, of Salerno, of Stalingrad, of Normandy and of Okinawa.

We are now on the eve of the Peace Conference. Ethiopia has given proof of great tolerance towards an enemy that for sixty years has brought her such untold miseries and loss. Thousands of enemy nationals live out peaceful lives amongst us. We have supported the decision to grant the assistance of the United Nations Relief and Rehabilitation Administration to Our vanquished enemy although such aid to Ethiopia the victim of aggression has been infinitesimal. As one of the United Nations We agree to the principles of working in peace with Our former enemies. However, that collaboration must be based on good faith and mutual confidence. Ethiopia has demonstrated and will continue to demon-



www.ethiopianorthodox.org

*strate her good faith inspite of bitter deceptions from those who have abused of it. It is then for the enemy to proffer the hand of friendship. If he wishes the friendship of Ethiopia he must, however, sincerely repent of sixty years of injustices and declare himself prepared to rectify them. If that gesture is accompanied by the firm desire to work in peace without those thoughts of aggression which have motivated and guided Italian policies for sixty years, Ethiopia will accept that gesture in a spirit of friendship and mutual comprehension.*

*We will now turn to the period of peace at which we have, by the Grace of God, at last arrived. It is necessary that the Governments of the United Nations who are now working for the reconstruction of World Peace should be guided by the principle of impartiality so that they shall lay down a solid and proper foundation stone for a system of peace which shall out live generations.*

*If the condition of the peace is such as will satisfy the conscience and sense of justice of men, if it is assured to human kind that they shall toil and live happily*



*under a just system in which no discrimination will be made between small and great, then the peace system that shall be laid down can leave a heritage for the coming generation which will be full of happy life and boundless prosperity.*

*We hope that the future generation will realize the magnitude of sacrifices that was required to accomplish all the works, that is in particular our duty to achieve for Ethiopia as well as the work of just peace so that it may preserve it as gain.*

*Although Ethiopia was among the ancient civilized nations it is understood that she must struggle to take her place among the civilized nations of today. Modern culture is not a new vogue to Ethiopia, the door is wide open to her. All she needs are institutions and schools to filter and assimilate her ancient culture with modern culture.*

*As you all know, before Ethiopia was invaded by the enemy we have done all that could be done to advance education in spite of all the difficulties that had to be encountered.*



www.ethiopianorthodox.org

*The products of our schools have been put to trial both in peace time as well as in time of Ethiopia's calamity. At this moment let us remember all those who have been hunted and murdered by the enemy.*

*Humanity by nature is gifted to think freely, but in order that his free thought should lead him to the goal of liberty and independence his way of thinking must be shaped by process of education. It is understood that the independence of mind created by education individually will have as result the creation of independently minded nation.*

*When we compare the numbers of schools functioning in Ethiopia today with those that existed before the occupation of the enemy, we can view with keen satisfaction the advance achieved within the past five years. We are sowing seeds on fertile soil and schools are springing up throughout the land attended by a youth of today who is thirsty for knowledge.*

*At present there are numerous schools in function attended with thousands of youths. A large number of these youth are already showing sign that they shall some day be useful servants of Ethiopia. From amongst these*



*will be chosen intelligent youth of worthy character to be sent abroad to complete their education. In addition We hawe founded special schools for the training of Cadets and Police as well as a school for aviation in order to help the good functioning of administration. We have not limited our education program to what has already been achieved, on the contrary we are doing all we can to open thousands of additional schools all over the Empire. Preparation is well under way for the opening of a large University at Addis Ababa.*

*Education, work and diligence are the main foundation of our national existence. We call upon all Ethiopians to send their children to the nearest school, for, it is suicide and a crime against responsibility which God places in all parents not to educate one's own children.*

*The catastrophe which was brought about by human hand during the past years can be avoided in the future by religion and hope in God which should be in the heart of the People. And this can be achieved by education which if not borne by the youth, the effort which is made for peace will be in vain.*

*We hope that at the Conference of the Peace which will be held in the near future those who will be responsible shall be inspired with profound idea of justice towards human cause and rights.*



www.ethiopianorthodox.org

ስለ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፶፬ኛ ፡ ዓመት ፡ የልደት ፡ በዓል ፡ አከባበር ፡ የከተማው ፡ ገዥ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ።

## ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ።

ይህችን ፡ የተከበረችና ፡ የተቀደሰች ፡ በዓለ ፡ ልደትዎን ፡ ለማክበር ፡ ምክንያት ፡ አግኝተው ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ የተሰበሰቡ ፡ ተወዳጅ ፡ አገልጋይዎችዎና ፡ ሕዝበችዎ ፡ ስም ፡ ከልባቸው ፡ ያለውን ፡ የበዛ ፡ ደስታ ፡ ለባለሙሉቃቸው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እንድገልጽ ፡ ክብር ፡ በማግኘቴ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ታላቅ ፡ ቸርነት ፡ ደስታዬ ፡ የበዛ ፡ ነው ።

## ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፤

በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለሚናፈቀው ፡ የሕይወት ፡ ዘመንዎ ፡ የዛሬዩቱ ፡ የተባረከች ፡ ቀን ፡ ሕዝብዎ ፡ ፶፬ኛው ፡ ዘመንዎ ፡ በመምላቱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገነ ፤ ፶፭ኛውም ፡ ዘመን ፡ እንዲሁ ፡ በደስታና ፡ በጤና ፡ መፈጸሙን ፡ ያሳየን ፡ እያለ ፡ ከልሂቅ ፡ እስከ ፡ ደቂቅ ፡ ልመናውን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚገልጽበት ፡ ቀን ፡ ናት ።

ግርማዊነትዎንም ፡ እንኳን ፡ ከዚህ ፡ አደረሰዎ ፡ እላለሁ ።



እንኳን ፡ ይህን ፡ ለማየት ፡ አበቃዎ ፡ ስል ፡ ነው ፤ እንዲህም ፡ ያልኩት ፡ ከቶ ፡ የማይዘነጋው ፡ የጠላቶቻችን ፡ ሁኔታ ፡ ትዝ ፡ እያለኝ ፡ ነው ።

ባለፉት ፡ ፭ት ዓመታት ፡ የተደረገልዎን ፡ ተአምር ፡ ልለፈውና ፡ በዚሁ ፡ በያዝነው ፡ ዓመት ፡ በኢጣሊያ ፡ ንጉሦች ፡ የተደረገውን ፡ ብቻ ፡ ልናገር ።

የግርማዊነትዎን ፡ ዙፋን ፡ ደርበ ፡ በቂማርነት ፡ ሊኖር ፡ የተመኘው ፡ የኢጣሊያ ፡ ንጉሥ ፡ ዛሬ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?

በአረመኔነት ፡ ጭከና ፡ በደረገው ፡ የመሣሪያ ፡ ብልጫ ፡ ስለ ፡ ሀገርዎና ፡ ሕዝብዎ ፡ ከሀገሩዋ ፡ በኀዘን ፡ በተሰደዱ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ሀገርዎን ፡ ቀምቶ ፡ ሊኖር ፡ የተመኘው ፡ ንጉሥ ፡ ዛሬ ፡ ወዴት ፡ ሔደ ፡ ?

ይህም ፡ ዝርዝሩ ፡ ለዐዋቂዎች ፡ የተሰወረ ፡ ባይሆን ፡ ለማያውቁት ፡ በጭሩ ፡ እንዳስረዳቸው ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ይፍቀዱልኝ ።

ነገሩ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤ ኢጣሊያ ፡ ድል ፡ ከሆነች ፡ ጀምሮ ፡ ሕዝቦቿ ፡ ከሁለት ፡ ተከፍለው ፡ከመበጣበጥ ፡ አላረፉም ።

በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ የኢጣሊያ ፡ ንጉሥ ፡ እንደሙሶሊኒ ፡ የገዛ ፡ ሕዝቦቹ ፡ እንዳይገድሉት ፡ ከዙፋኑ ፡ ወርዶ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ተሰደደ ።



www.ethiopianorthodox.org

ያልታደለው ፡ አልጋ ፡ ወራሹ ፡ ባባቱ ፡ አልጋ ፡ ቢቀመጥ ፡ እንኳ ፡ የሕዝቡ ፡ ጥላቻ ፡ እየበረታ ፡ ሄዷልና ፡ በ፳፱ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ከዙፋኑ ፡ ሻሩት ፤ ይህ ፡ አልበቃ ፡ ብሏቸው ፡ ሊገሉት ፡ ስለ፡ፈለጉት፡ቤተ፡ሰቦቹን፡ ይዞ ፡ ወደ ሌላ ፡ አገር ፡ ተሰደደ ፤ አሁን ፡ ኢጣሊያ ፤ ንጉሥ ፡ የሌላት ፡ ሆናለች ።

ደግሞም ፡ በኛ ፡ ክፉ ፡ የመከሩ ፡ የመንግሥቱ ፡ አለቆች ፡ በጥፋታችንም ፡ ደስ ፡ ያላቸው፡ሁሉ ፡ ንብረታቸው ፡ ተወርሶ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተላልቀው ፡ ዛሬ ፡ ከዚች ፡ ዓለም ፡ ብዙዎች ፡ የሉም ። ይህ ፡ ነው ፡ የእግዚአብሔር ፡ እውነተኛ ፡ ፍርድ ።

የጠላቶቹን ፡ አወዳደቅ ፡ ያየ ግርማዊነትዎ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ።

እንኳን ፡ ግርማዊነትዎን ፡ ስለኛ ፡ እዚህ ፡ አደረሰልን ፤ ይህንንም ፡ ማለቴ ፡ ለኛና ፡ ለሀገርዎ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ የሚያደርጉትን ፡ መሥዋዕትነት ፡ በመገንዘብ ፡ ነው ፤ ዝርዝሩም ፡ በኔ ፡ አንደበት ፡ ተነግሮ ፡ አያልቅም ።

ለሀገራቸው ፡ ጥፋት ፡ ለሕዝባቸው ፡ ውርደት ፡ የተፈጠሩ ፡ ንጉሦችና ፡ መሪዎች ፡ በዘመናችን ፡ እንኳን ፡ ብዙ ፡ አየን ።

ለኛ ፡ ግን ፡ ደም ፡ ተበቃይ ፤ አገሩን ፡ ሕዝቡን ፡ የሚ



ያከብሩ ፡ ንጉሥ ፡ አባት ፡ መምህር ለሰጠን ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ይሁን ።

## ግ ር ማ ዊ ፡ ሆ ይ ።

ባርያዎ፡ዛሬ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ፊት ፡ ሞገስ ፡ አግኝቻለሁና ፡ ጥቂት ፡ ልቀጥል ፡ ይፈቀድልኝ ! ።

መቼም ፡ በማይዘነጋው ፡ በደረሰብን ፡ የጭንቅ ፡ ዘመናት ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ባልኖሩበት ፡ ጊዜያት ፤ ለኢትዮጵያም ፡ የሕዝብዎና ፡ የሀገርዎ፡የመዳን ፡ ተስፋ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ በሕዝቦችዎ ፡ ፊት ፡ ደጋግሞ ፡ መናገርን ፡ እወዳለሁ ።

## ጃ ን ሆ ይ ።

አርበኞችዎ ፡ ከጨካኙ ፡ ጠላት፡ጋር ፡ ትግላቸውን ፡ በሚያስደንቅ፡ሁኔታ ፡ የቀጠሉ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ተስፋ ፡ ነው ። የሕይወታቸውም ፡ ብርታት ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ትንፋሽ ፡ ነበረና ፡ ዘወትር ፡ መጋደልን ፡ አልሰለቹም ።

ስደተኞች ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ እንደሚመልሷቸው ፡ ግርማዊነትዎን ፡ ተስፋ ፡ ( ሥንቅ ) ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ አገር ፡ ተሰደዱ ። በስደታቸውም ፡ አገር ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ተስፋ ፡ ይጽናኑ ፡ ነበር ።

በጨካኙ ፡ ጠላት ፡ መንጋጋ ፡ መኻል ፡ የነበሩት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የጠላታቸውን ፡ ጥርስ ፡ ሰብረው ፡ እንደሚያወጡዋ



www.ethiopianorthodox.org

ቸው ፣ ግርማዊነትዎን ፣ ተስፋ ፣ አድርገው ፤ ጭንቀትን ፣ ሁሉ ፤ በትዕግሥት ፣ ተሸከሙ ።

በተቀደሰው ፣ መጋደል ፣ ከዚህ ፣ ዓለም ፣ በሞት ፣ የተነጠሉም ፣ ዓፅማቸው ፣ ከነጻ ፣ አገራቸው ፣ ጋራ ፣ ነጻ ፣ እንደሚወጡ ፣ በግርማዊነትዎ ፣ ላይ ፣ ተስፋቸውን ፣ አሳርፈው ፣ ከመቃብር ፣ ውጪ ፣ ዘለዓለም ፣ አንቀላፉ ።

ቃሉ ፣ በግድም ፣ በውድም ፣ ለጠላት ፣ መሣሪያ ፣ ሆነው ፣ የነበሩት ፣ እንኳን ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ ከዚህ ፣ እርግማን ፣ እንደሚያወጡዋቸው ፣ ግርማዊነትዎን ፣ ተስፋ ፣ አድርገው ፣ ነበር ።

በሁለት ፣ ወገን ፣ የጦር ፣ መጋጫ ፣ የሆኑት ፣ ባላገሮች ፣ ግርማዊነትዎን ፣ ተስፋ ፣ በማድረግ ፣ ሥቃያቸውን ፣ በትዕግሥት ፣ ተሸከሙ ።

እውነትም ፣ ግርማዊነትዎ ፣ ለሀገርዎና ፣ ለሕዝብዎ ፣ ተስፋ ፣ ኑረዋልና ፣ ማናቸውም ፣ አልተሳሳቱም ፤ የእግዚአብሔር ፣ ፈቃድ ፣ እንደ ፣ ሰው ፣ ምኞት ፣ እንዲሆን ፣ ስላልፈቀደ ፤ የሁላችንንም ፣ ተስፋ ፣ ፈጻሚው ፣ ግርማዊነትዎ ፣ ሆነ ።

ጠላት ፣ ጠፋ ፣ እኛም ፣ ዳንን ፤ ይህም ፣ ለኛና ፣ ለዓለም ፣ አስደናቂ ፣ ተአምር ፣ ሆነ ፤ ምስጋናው ፣ ለእግዚአብሔር ፣ ብቻ ፣ ይሁን ።



ዘመኑ ፣ አሮጌ ፣ ሲሆን ፣ በግርማዊነትዎ ፣ አዲስ ፣ ዘመን ፣ ተባለ ፤ ቀዳማዊው ፣ ልደትዎም ፣ ሁለተኛ ፣ ልደት ፣ ሲደርብ ፤ ከኢትዮጵያ ፣ ሁለተኛ ፣ ልደት ፣ ጋር ፣ የተሳሰረ ፣ ሆነ ። ይህንስ ፣ ግርማዊነትዎ ፣ ለኢትዮጵያ ፣ ዳግም ፣ ልደት ፣ የለወጠው ፣ አይደለምን ።

ስለዚህ ፣ የዛሬዋን ፣ ቀን ፣ የሀገራችንና ፣ የግርማዊነትዎ ፣ ዳግም ፣ ልደት ፣ ቀን ፣ ናት ፣ እያልን ፣ በአንድ ፣ ላይ ፣ እናከብራታለን ።

ግርማዊነትዎ ፣ ስለዚህ ፣ ለዚህ ፣ ትውልድ ፣ መድኅን ፣ ለመሆን ፣ በዛሬ ፣ ቀን ፣ ተወለዱልን ፤ የተወለዱበትንም ፣ ተግባር ፣ ፈጽመዋል ።

ግርማዊነትዎ ፣ ግን ፣ ገና ፣ ዕለት ፣ ዕለት ፣ ለሀገሩና ፣ ለሕዝቡ ፣ ሌትና ፣ ቀን ፣ ይደክማል ፤ የወዙም ፣ ፍሬ ፣ ደስ ፣ ያሰኘዋልና ፤ ስለዚህ ፣ በየዕለቱ ፣ መንፈሳዊ ፣ ኃይል ፣ እየጨመረ ፣ ይሄዳል ።

አሁንም ፣ የኛና ፣ የኢትዮጵያ ፣ ተስፋ ፣ በግርማዊነትዎ ፣ ላይ ፣ ነው ፤ ከዘመንዎ ፣ በፊት ፣ በጠላት ፣ ኃይል ፣ ከእናት ፣ አገራቸው ፣ የተነጠሉ ፣ ወንድሞቻችን ፣ ተስፋቸው ፣ በግርማዊነትዎ ፣ ላይ ፣ ነውና ፣ ሁሉን ፣ የሚችለው ፣ ፈጣሪ ፣ እንዲፈጽምልዎ ፣ አንጠራጠርም ፤ ስለዚህ ፣ ሁሉ ፤ የማይቸግረውን ፣ ዕድሜ ፣ አይንሳዎ ፣ እያልን ፣ እግዚአብሔርን ፣ እንለምነዋለን ።



www.ethiopianorthodox.org

ግርማዊ ፡ ሆይ ፤

ልዑል ፡ ፈጣሪ ፡ ድንቅ ፡ የሆነውን ፡ ትልቅ ፡ ተአምር ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ አድርጓልና ፤ ከእንግዴህ ፡ ወዲያ ፡ እኛ ፡ ብቻ ፡ ሳንሆን ፡ ትውልድ ፡ ሁሉ ፡ ያመሰግንዎታል ።

ከእግዚአብሔር ፡ በተሰጠዎ ፡ ጸጋ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ይደነቅብዎታል ፤ አባት ፡ መምህር ፡ እንደ ፡ ልቡ ፡ ፈቃዱን ፡ ፈጻሚ ፡ የሆነለትን ፡ ንጉሥ ፡ መርጦ ፡ ስለ ፡ ሰጠንም ፡ እግዚአብሔርም ፡ ይመሰገናል ።

አሁንም ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ስለሚወዳቸው ፡ ሲል ፡ ያልቸገረውን ፡ ዘመን ፡ አይንፈግብን ።

በአለፈው ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ደስ ፡ እንደ ፡ ተሰኘን ፡ ወደፊታችን ፡ የተደቀነውን ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ድካም ፡ ተፈጽሞ ፡ ለማየት ፡ ያብቃን ።

ወደፊት ፡ መልካሙን ፡ ዕድል ፡ ጤናንትን ፡ ከደስታ ፡ ጋር ፡ ረጅም ፡ ዘመን ፡ ለግርማዊነትዎና ፡ ንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ይስጥልን ።

የወንድነትና ፡ የመተባበር ፤ የመሥራት ፡ መንፈስ ፡ ለሕዝባችን ፡ አይንሳ ።

ኢትዮጵያንም ፡ ለግርማዊነትዎና ፡ ለዘርዎ ፡ ውለታ ፡ መላሽ ፡ ያድርግ ።



www.ethiopianorthodox.org